ቀን ______________________

# <u>የውክልና ስልጣን ማስረጃ</u>

ወካይ:- ___________________________

አድራሻ:- ___________________________

___________________________

ተወካይ:- ___________________________

አድራሻ:- ___________________________

___________________________

እኔ ወካይ ለተወካይ የምንሰጣቸው የውክልና ስልጣን ተወካይ አንደእኔ በመሆን የሟች __________________________________ ከዚህ አለም በሞት መለየት ምክንያት ወራሽነቴን በማንኛውም ፍ/ቤት ቀርበው እንዲያረጋግጡ ውርስ አጣሪ እንዲያሾሙ ካረጋገጡም በኋላ በውርስ የማገኘውን የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲሁም በማንኛውም ባንክ ቤት ውስጥ በሟች _____________________ ስም ያለውን ገንዘብ የድርሻዬን ፈርመው እንዲቀበሉ፣ ስሙን ወደስሜ እንዲያዞሩ፣ እንደእኔ በመሆን በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን ማንኛውም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲጠብቁ ፣ እንዲቆጣጠሩ ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ የኪራይም ሆነ የኮንትራት ገንዘብ ተሳስበው እንዲቀበሉ፣ ውል እንዲያፈርሱ፤ በስሜ የተዋዋልኳቸውን የኪራይም ሆነ ማንኛውም አይነት ውሎች ተወካይ እንዲያድሱ ማፍረስ እንዲችሉ፣ በስሜ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ ሰነድ መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ገንዘብ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ ማንኛውንም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ግብር እንዲገብሩ፣ በስሜ የግንባታና የእድሳት ፈቃድ እንዲያወጡ፣ ለግንባታ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችንም ሆነ ሲሚንቶ እንዲገዙ፣ የግንባታ ስራ እንዲያካሂዱ፣ ካርታ እንዲያወጡ፣ በኢትዮቴሌኮም በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እየቀረቡ፣ በስሜ ውል ተዋውለው ውሃ መብራት ስልክ እንዲያስገቡ፣ ውሃ ፣ መብራት፣ ስልክ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ መንጃ ፍቃድ እንዲያሳድሱ፣ ሊብሬ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ ቢጠፋ እንዲያዘጉና እንዲያስከፍቱ፣ በስሜ በማንኛውም ባንክ ተመዝግቦ የሚገኘውን የባንክ አካውንቴን እንዲያንቀሳቅሱ፣ ገንዘብ ገቢና ወጪ እንዲያደርጉ፣ በስሜ ቼክ ፈርመው መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ቼክ እንዲመነዝሩ፣ በስሜ የሚሰጠኝን የካሳ ክፍያ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልተው እንዲቀበሉ፣ በስሜ ማንኛውም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ከማንኛውም ተቋም የትምህርት የልደት የምስክር ወረቀት ያላገባ ስለመሆኔ ማስረጃዎችን  እንዲያወጡ ማረጋገጫ እንዲያስሙቱ መልቀቂያና ክሊራንስ መሸኛ እንዲያወጡ በአጠቃላይ በመንግስታዊ መ/ቤትም ሆነ ህዝባዊያን ድርጅቶች አስተዳደር መ/ቤት በአገር ውስጥ ገቢ፣ በክ/ከተማ በቀበሌ፣ ወረዳ ከተማ ልማት፣ በመሬት አስተዳደር በመንገድ ትራንስፖርት፣ በጤና ቢሮ፣ በኤምባሲ፣ በኢሚግሬሽን፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በኪራይ ቤቶች፣ በቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ በፖስታ ቤት፣ በንግድና ኢንዱስትሪ፣ በማዘጋጃ ቤት፣ በኢንቨስትመንት ቢሮ፣ በከተማ  ልማት፤ ትምህርት ሚኒስቴር፣ በፍ/ቤት እየቀረቡ ያለኝን ጉዳይ ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፤ በማንኛውም ቦታዎች ላይ እንደእኔ ተጠሪ እንዲሆኑ፣ በስሜም ሆነ በንብረቴ ላይ ክስ ክርክር ቢነሣ የሕግ ጠበቃ ወክለው በማንኛውም ፍ/ቤት በመቅረብ እንዲከራከሩ መልስ እንዲሰጡ ቃለ መሀላ እንዲያቀርቡ አፈፃፀም እንዲከታተሉ ማረጋገጫ እንዲፈርሙ ይግባኝ እንዲጠይቁ ውሳኔ እንዲቀበሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ውክልና መስጠትም ሆነ መሻር እንዲችሉ ይህንን ሙሉ የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 58/ሀ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2199/2205 መሠረት መስጠቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የወካይ ስምና ፊርማ

___________________________

ቀን ____________________

<u>**የውክልና ስልጣን ማስረጃ**</u>

1. ወካይ:- ______________________
   አድራሻ:- ______________________
   ______________________

2. ወካይ:- ______________________
   አድራሻ:- ______________________
   ______________________

ተወካይ:- ______________________
አድራሻ:- ______________________
______________________

እኛ ወካዮች ለተወካይ የምንሰጣቸው የውክልና ስልጣን ተወካይ አንደእኛ በመሆን የሟች ______________________ ከዚህ አለም በሞት መለየት ምክንያት ወራሽነታችንን በማንኛውም ፍ/ቤት ቀርበው እንዲያረጋግጡ ውርስ አጣሪ እንዲያሾሙ ካረጋገጡም በኋላ በውርስ የምናገኘውን የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲሁም በማንኛውም ባንክ ቤት ውስጥ በሟች ______________ ስም ያለውን ገንዘብ የድርሻችንን ፈርመው እንዲቀበሉ፣ ስሙን ወደስማችን እንዲያዞሩ እንደእኛ በመሆን በስማችን ተመዝግቦ የሚገኘውን ማንኛውም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲጠብቁ ፣ እንዲቆጣጠሩ ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ የኪራይም ሆነ የኮንትራት ገንዘብ ተሳስበው እንዲቀበሉ፣ ውል እንዲያፈርሱ፤ በስማችን የተዋዋልናቸውን የኪራይም ሆነ ማንኛውም አይነት ውሎች ተወካይ እንዲያድሱ ማፍረስ እንዲችሉ፣ በስማችን ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ ሰነድ መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ገንዘብ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ ማንኛውንም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ግብር እንዲገብሩ፣ በስማችን የግንባታና የእድሳት ፈቃድ እንዲያወጡ፣ ለግንባታ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችንም ሆነ ሲሚንቶ እንዲገዙ፣ የግንባታ ስራ እንዲያካሂዱ፣ ካርታ እንዲያወጡ፣ በኢትዮቴሌኮም በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እየቀረቡ፣ በስማችን ውል ተዋውለው ውሃ መብራት ስልክ እንዲያስገቡ፣ ውሃ ፣ መብራት፣ ስልክ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ መንጃ ፍቃድ እንዲያሳድሱ፣ ሊብሬ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ እንዲያወጡ፣ ሲም ካርድ ቢጠፋ እንዲያዘጉና እንዲያስከፍቱ፣ በስማችን በማንኛውም ባንክ ተመዝግቦ የሚገኘውን የባንክ አካውንታችንን እንዲያንቀሳቅሱ፣ ገንዘብ ገቢና ወጪ እንዲያደርጉ፣ በስማችን ቼክ ፈርመው መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ቼክ እንዲመነዝሩ፣ በስማችን የሚሰጠኝን የካሳ ክፍያ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አማልተው እንዲቀበሉ፣ በስማችን ማንኛውም ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ከማንኛውም ተቋም የትምህርት የልደት የምስክር ወረቀት ያላገባ ስለመሆናችን ማስረጃዎችን እንዲያወጡ ማረጋገጫ እንዲያስሙቱ መልቀቂያና ክሊራንስ መሸኛ እንዲያወጡ በአጠቃላይ በመንግስታዊ መ/ቤትም ሆነ ህዝባዊያን ድርጅቶች አስተዳደር መ/ቤት በአገር ውስጥ ገቢ፣ በክ/ከተማ በቀበሌ፣ ወረዳ ከተማ ልማት፣ በመሬት አስተዳደር በመንገድ ትራንስፖርት፣ በጤና ቢሮ፣ በኤምባሲ፣ በኢሚግሬሽን፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በኪራይ ቤቶች፣ በቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ በፖስታ ቤት፣ በንግድና ኢንዱስትሪ፣ በማዘጋጃ ቤት፣ በኢንቨስትመንት ቢሮ፣ በከተማ ልማት፤ ትምህርት ሚኒስቴር፣ በፍ/ቤት እየቀረቡ ያለንን ጉዳይ ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፤ በማንኛውም ቦታዎች ላይ እንደእኛ ተጠሪ እንዲሆኑ፣ በስማችንም ሆነ በንብረታችን ላይ ክስ ክርክር ቢነሣ የሕግ ጠበቃ ወክለው በማንኛውም ፍ/ቤት በመቅረብ እንዲከራከሩ መልስ እንዲሰጡ ቃለ መሀላ እንዲያቀርቡ አፈፃፀም እንዲከታተሉ ማረጋገጫ እንዲፈርሙ ይግባኝ እንዲጠይቁ ውሳኔ እንዲቀበሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ውክልና መስጠትም ሆነ መሻር እንዲችሉ ይህንን ሙሉ የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 58/ሀ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2199/2205 መሠረት መስጠታችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

የወካዮች ሙሉ ስምና ፊርማ

1 ____________________

2 ____________________